بسم الله الرحمن الرحيم

ለአሏህ መኖሩ ማስረጃው ምንድን ነው ?

ባሪያዎችን የፈጠረበት ምክኒያት እና ጥበቡ ምንድን ነው ?

መልስ

የአሏህ መኖርማ ለተገነዘበው በጣም ግልፅ ነው በርካታ ጥናት እና ምርምር የሚያስፈልገው ጉዳይም አይደለም

ስናስተነትነው የፈጣሪን መኖር (በሶስት) ማስረጃዎች በቀላሉ ማወቅ ይቻላል

1/ተፈጥሯዊይ ማስረጃዎች

2/በስሜት ህዋሳት የምንደርስባቸው ማስረጃዎች

3/ ሸሪዐዊይ (ሀይማኖታዊይ) ማስረጃዎች ናቸው

ተፈጥሯዊይ ማስረጃ ያልናቸው ለምሳሌ ማንኛውም ሰዉ በራሱ ተነሳሽነት ፈጣሪ እንዳለው ውስጡ ማወቁ እና ማመኑ

የሰው ልጅ ከፍተኛ ጭንቀት በገጠመው ጊዜ

ከጌታው እገዛን በመፈለግ ልቦቹ  እጆቹና አይኖቹ ወደሰማይ መዞራቸው እና የመሳሰሉት ይገኙበታል

አሏህ ሱበሃነሁ ወተዓላ እንዲህ ይላል

فَأَقِمْ وَجْهَكَ لِلدِّينِ حَنِيفًا ۚ فِطْرَتَ ٱللَّهِ ٱلَّتِى فَطَرَ ٱلنَّاسَ عَلَيْهَا ۚ لَا تَبْدِيلَ لِخَلْقِ ٱللَّهِ ۚ ذَٰلِكَ ٱلدِّينُ ٱلْقَيِّمُ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعْلَمُونَ

ወደእውነት ተዘንባይ ሁነህም ፊትህን ለሀይማኖት ቀጥ አድርግ  የአሏህን ፍጥረት ያችን  አሏህ ሰዎችን በእርሷ ላይ የፈጠረባትን (ሀይማኖት ያዛት) የአሏህን ፍጥረት የሚለውጥ የለም ::ይህ ቀጥተኛ ሀይማኖትነው ግን አብዛሀኛዎቹ ሰዎች አያውቁም

በስሜት ህዋሳቶች የሚደረስባቸው ማስረጃዎች ያልናቸውማ ፤

እዚህም እንደምሳሌ በአለማችን ላይ የሚከሰቱ ክስተቶች ይገኙበታል ይህም በዙሪያችን የምትገኘዉ አለም በርካታ ክስተቶችን ማስተናገዷ የማይቀር ጉዳይ ነው

ከነዚህም ከባባድ ክስተቶችም መካከል በመጀመሪያ የሚጠቀሰው የነገራቶች የመፈጠር ክስተት ነው ::  ሁሉም ነገራቶች  የዛፎች የድንጋዮች የሰው ልጆች የመሬቶች

የሰማዮች የባህሮች እና የወንዞች መከሰት እና መፈጠር ይገኝበታል ::

እነዚህ እና ሌሎች በርካታ ፍጥረታት መኖራቸው እውነት ነው

ግን ለመሆኑ እነዚህን ሁሉ የፈጠራቸው የተንከባከባቸው የሚያስፈልጋቸውን የሚያሟላላቸው ለመኖራቸውም ዋስትና የሚሰጣቸው ማን ነው ? የሚል ጥያቄ ቢነሳ

መልስ

ወይ እንዲሁ በድንገት ነው ያለምንም ምክኒያት የተገኙት  እንዲህ ከሆነ ደግሞ እነዚህ ነገራቶች እንዴት እንደተገኙ እና እንደተፈጠሩ ማወቅ አይቻልም

ወይም እነዚህ ነገራቶች እራሳቸውን ፈጥረዋል  እራሳቸውንም በራሳቸው  ተንከባክበዋል

ወይም የፈጠራት ፈጣሪ ያስገኛት አስተናባሪ አለ

እነዚህን ሶስት ሙግቶች ስንመለከት

ፍጥረታት ያለ ፈጣሪ መገኘታቸውም ሆነ እራሳቸውን መፍጠራቸው ውድቅ ሙግት ሁኖ እናገኘዋለን::

እነዚህ ሙግቶች ውድቅ ከሆኑ ደግሞ

አሏህ መኖሩ እና የፈጠራቸውም እሱ መሆኑ ፍንትው ያለ ሀቅ ሁኖ እናገኘዋለን

የፈጠረም ለፍጥረታት የሚበጃቸዉን የሚያደርግላቸውም እርሱ አሏህ ነው

ለመኖራቸውም ዋስትና የሚሰጣቸው እርሱ ነው

ይህም ልክ አሏህ በዚህ በቁረአኑ ካሰፈረው መልእክት ጋር አንድ ነው :

አሏህ እንዲህ ይላል

﴿أَمْ خُلِقُوا مِنْ غَيْرِ شَيْءٍ أَمْ هُمُ الْخَالِقُونَ﴾
[سورة الطور: 35]

أَمْ خَلَقُوا السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ ۚ بَل لَّا يُوقِنُونَ

(ወይስ ያለ አንዳች ፈጣሪ ተፈጠሩን ?ወይስ እነርሱ ፈጣሪዎች ናቸውን?ወይስ ሰማያትና ምድርን ፈጠሩን?አይደለም አያረጋግጡም

ሸሪዐዊይ ማስረጃዎች ያልናቸው

ሸሪዐዊይ ድንጋጌዎች መኖራቸው ነው

ሸይኽ ኢብኑ ዑሠይሚን እንዲህ ይላሉ ሸሪዐዊይ ብያኔዎች እና ድንጋጌዎች ሁሉ የፈጣሪን መኖር የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች ናቸው  እንዲሁም የእውቀቱን የጥበቡን የእዝነቱን ምሉዕነት የሚያረጋግጡ ናቸው ምክኒያቱም

በእነዚህ ምሉዕ ድንጋጌዎች ምሉዕ እና ፍፁም የሆነ ደንጋጊ ያስፈልጋቸዋል

ይህ ፍፁም ከጉድለት የፀዳ በያኝ እና ደንጋጊ ደግሞ አሏህ ሱበሃነሁ ወተዓላ ነው ::

አሏህ ለምን ፈጠረን ለሚለው ጥያቄማ መልሱ

በብቸኝነት እንድናመልከው

እንድናወድሰው እና እንድንዘክረው

እንዲሁም ያዘዘንን ነገራቶች በሙሉ እንድንተገብር ነዉ

በዚህም ያዘዘን መንገዱን እና ህይማኖቱን ግልፅ ካደረገልን በኋላ ነው

አሏህ እንዲህ ይላል

{ وَمَا خَلَقْتُ الْجِنَّ وَالْإِنْسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ }

(ጋኒንን እና ሰውንም ሊያመልኩኝ እንጅ ለሌላ አላማ አልፈጠርኳቸውም )